# አፈርኩባችሁ--የዲያስፖራ ዜጎች

በውጭ ሀገር በተለይም በሰሜን አሜሪካ ባሉ አያሌ ኢትዮጵያውያን እያፈርን መሆናችም መግለጫው ጊዜ ነው:: ዝም ዝሙ አላዋጣም:: ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ እየሄዱ በገንዝብ ኃይል በሕፃናት እህቶቻችንና ልጆቻችን፣ወገኖቻችን ላይ የሚጫወቱትን አረመኔዎች በተመለከተ ወደፊት ከነስማቸው የምምለስበት ይሆናል:: ዛሬወ ማተኮር የፈለግኩት በሁለት ጉዳዮች ላይ ነው:: በማዕቀብና በርስ በርስ መጠላለፉና ሻጥር ላይ ::

ማዕቀብ በወያኔ ላይ ይደረግ እየተባለ ባለበት የዚህ ማዕቀብ ዋና ደጋፊ ነን ፣ ፀረ ወያኔ ነን፣ ለቴዲ አፍሮ አልቃሽ ጯኺ ነን የሚሉ አስመሳዮች ግን በጀርባ ከወያኔ ጋር ገጥመው እንዳሉ መጋለጥ ያለበት ጉዳይ ሆኗል:: በአዜብ ጎላ የመለስ ሚስት፣በአባ ገብረመድህን (አቡነ ጳውሎስ ባዩኝ በሚለው ካድሬና) ሌሎችም ባለቤትነት የተቋቋመው (በሳሙኤል የይፋ ባለቤትነት) ሰንሻይን ኩባንያ በቅርቡ በሰጠው መግለጫ በብዛት የሰራቸው ቤቶችና ቪላዎች 70 በመቶ ገዢዎቹ ከውጭ የመጡ የኢትዮጵያ ተወላጆች ሲሆኑ ከነዚሁም 50 በመቶ በላይ ከአሜሪካ የመጡ መሆናቸውን አስታውቋል:: ለወያኔ ያውም በቀጥታ ለመለስ ሚስት በሚሊዮን ዶላርና ብር እየሰጡ ያሉት ከባዕድ ሀገር በተለይም ከአሜሪካ ቤት እንግዛ እያሉ የሚመላለሱት ዜጎች መሆናቸውን ወያኔ ራሱ አብስሮናል ማለት ነው!! አያሳፍርም? ቤት ግዢ ንግድ እያሉ ለወያኔ ገንዘብ እየገበሩ የሀገርና የሕዝብ መከራን እያባዙና እየጨመሩ ያሉትን ማንነት ማጋለጥ ተገቢና ወቅታዊ ነውና ከውግዘት ባሻገር ይህ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል:: ዛሬም በአየር መንገዱ እየተጓጓዙ ለወያኔ ሚሊዮን ብር ገቢ የሚሰጡ ዜጎች ብዙ ሲሆኑ አብዛኞቹ ደግሞ ከአሜሪካ መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል:: አዲዮስ ማዕቀብ?

ማዕቀብ ደጋፊ ነን እያሉ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን እርምጃ የሚሰርዙና ተቃዋሚ እርምጃ የሚወስዱ ጥቂቶች አይደሉም:: በአውሮጳና አሜሪካ የወያኔን ቢራና ወይን አምጥተው የሚሸጡ አሁንም አሉ--ገብቶ ቢራውንም፣ወይኑንም አምቦ ውሃውንም ጠጪውም ጥቂት አይደለም:: ፀረ ወያኔ ነኝ የሚለው ነፃነት ራዲዮ (ዋሺንግተን ዲሲ) የኢትዮጵያ አየር መንገድን ማስታወቂያ ያቀርባል:: የሻዕቢያው አፈ ቀላጤና የእነብርሀኑ ነጋ ደጋፊ ድረ ገፅ ሀላፊ ኤልያስ ክፍሌም ለ ቴዲ አፍሮ ጮሀኩ እያለ በጎን የወያኔውን ወናፍ ማህሙድ አህመድን ሲያትል ሄዳችሁ አጅቡ ይለናል:: መለስን ጠላሁ ቢልም የትግራይ የበላይነትን ደጋፊው አብርሃም በላይ (ኢትዮ ሚዲያ) ደግሞ የመቀሌ ኮሌጅን ማስታወቂያ ያስተናግዳል:: ወዘተ ወዘተ :: የጥቅም ጉዳይ ከሀገር ጥቅም ቀድሟል:: ሁሉንም ማጋለጥ በጣም አስፈላጊ ነው:: በመቻቻልና በአንጉል ምክንያቶች ድርደራ የሚሸፈን ሊሆን አይችልም:: በዚህ በኩል የማዕቀቡ አጋፋሪና ፀረ ወያኔ ነን እያሉ በሌላ በኩል ግን ወያኔ ላይ የሚደረገውን ማዕቀብ እየተፃረሩ ከወያኔ በዚህም በዚያም፣ በይፋም ሆነ በምስጢር ሲላላሱ ያሉትን በዝምታ ማለፍ አይገባም:: ይህን ስፅፍ ስንቱ ዜጋ የገናን በዓል ለማክበር እያለ ወደ ወያኔ በወያኔ

ቁጥጥር ስር ባለ አየር መንገድ ወደ አዲስ አበባ ሊጓዙ ተነስተዋል:: ገና አዲስ ዓመት በሚልም ለወያኔ ባደሩ ዘፋኞች ምሽትም ለመገኘት ቲኬት እየገዙ ናቸው::ታዲያ ማፈር ይነሰን?

ሌላው የዳያስፖራው ኢትዮጵያዊ ማፈሪያ የሆነው ፓል ቶክ በተባለው የእብዶች ገበያ ላይ በሚደመጠው አሳፋሪና አሳዛኝ ጫጫታ፣ተራ ዘለፋና ክስ ብቻ አይደለም:: በዚህ መድረክ በብዙ ቦታ አባወራ የሆኑት መህይሞች፣ተሳዳቢዎች፣ሰካራሞችና አደንዛዥ ዕፅ አጫሾች፣ ወያኔዎችና የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ያላቸው አዳማጭ በጣት የሚቆጠር በመሆኑ ከቁጥር ገብተው ለትችትም የሚበቁ አይደሉም:: ካስፈለገ ደግሞ የነዚህንም ታሪክና ጉድ ዘክዝኮ ማቅረብ ከባድ አይደለም:: ግን ለዚህ ፅሁፍ ያነሳሳኝ በመጪው ቅዳሜ ሊደረጉ የታሰቡ ስብሰባዎችን በሚመለከት ነው:: ሁሉም የአንድነተ ሀይል ነኝ እያለ አንዱ ሌላውን ለማደናቀፍና ለመነጠል ሩጫው መለስን ጫት የሚያስቅምና የሚያስመረቅን ሆኗል:: ዲሴምበር 21 መኢአድ ዶክተር ታየና አቶ አባይነህ ብርሃኑ የሕዝብ ስብሰባ ሲጠሩ በዚያው ጊዜ ሌሎቹ በቴዲ አፍሮ ስም ሌላ ዝግጅት አውጀዋል:: የሚገርመው ደግሞ ያውም የመኢአድ አባል ናቸው የሚባሉት ዶክተር አክሎግና መስፍን መኮንን የሚሳተፉበት ሌላ የሕዝብ ስብሰባ ተጠርቷል:: ምን ማለት ነው? ይህ እርስ በርስ መጠላለፍ ካልሆነ ምን ሊባል ይቻላል? ትላንት ኢሕአፓ ነበርን ይሉ የነበሩ ዛሬ ግን  የወያኔ አጫፋሪ በሆኑ አንጃዎች ፓል ቶክ ፀረ ኢትዮጵያ ጠባቦች ብቻ ሳይሆኑ በዚሁ ቡድን ሲወገዙ የነበሩትም ኢንጂኔር ሀይሉ ብቅ ብለዋል:: ምን ማለት ነው? ወዘተ ወዘተ ድብልቅልቅና ርስ በርስ መጠላላፍ መደነቃቀፍ:: ለወያኔ ማገዝ:: የሚታገሉት ላይ ሻጥርና ወራዳ ዘመቻን ማካሄድ::

አፈርኩባችሁ ወገኖቼ:: ሕዝብ ይህን ነው ከእኛ የሚጠብቀው? ለወያኔ ገንዘብ መለገስና ሕዝብን መርሳት? እርስ በርስ መነካከስና መሸጣጠር? ዛሬ በአንድነት ሀይል ድርጅቶችና መሪዎች ክፉ ዘለፋ የሚያካሂደው ወያኔ ነው ወይስ አንጃዎች፣ የብርሃኑ ነጋ ደጋፊ ድረ ገፆችና ሌላ ማፈሪያ ዘረኞችና ድብቅ ቅጥረኞች? መልሱ ግልፅ ነው:: ሀፍረታችን ተበራክቷል::

ገረመው ተማም
ከ አርሊንግተን